# መስጠት

መስጠት፡- ለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት፣ መጋቢነት፣ ገዢነት እውቅና መስጠት እና እርሱን የማክበርና የመፍራት ልምምድ ነው፡፡ ( ዘዳ 14፡23)

- ✓ እግዚአብሔር ከማንም ምንም ወስዶ፤ ወይም ተቀብሎ አያውቅም፡፡ ሁሉ የእርሱ ነውና፤ ( መዝ 50፡ 7-15)
- ✓ ስጦታውን ሳይሆን እርሱ የሚፈልገው ከእርሱ ጋር በትህትና መሄዳችንን ነው፡ ( ሚክ 6፡7)

## በአባቶች ዘመን

### አብርሃም

ከጦርነት ምርኮ ለሳሌም ንጉስ 1/10ኛ ስጦታ ሰጠው ( ዘፍ 14፡17)

- ✓ *አብርሃም ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ለእግዚአብሔር ካገኘው1/10ኛ ሲሰጥ አልተጻፈም*

### ይስሀቅ ፡-

### ያዕቆብ ፡- *የለመነው ቢፈጸምለት 1/10ኛ ለመስጠት ስእለት ተስሎ ነበር፡፡*

( ዘፍ 28፡18)

## በሕጉ ዘመን

### 1. በኩራት፡-

እግዚአብሔር ከሚሰጣቸው ሁሉ የመጀመርያውን ለራሱ መመለስ

- ✓ በአብዛኛው በተሰጣቸው ጊዜ ሁሉ ስለሚፈጸም ቶሎ ቶሎ ወይም ወቅቱን ጠብቆ የሚፈጸም ነበር

ዓላማው፡-

- ✓ ሁሉንም የሚሰጣቸው አምላካቸው እግዚአብሔር መሆኑንእንዲያስታውሱ ፤ እና ለሰጦታው አክብሮት መስጠት (ምሳ 3፥9-10)

- ✓ አምላካቸውን ከተሰጣቸው ነገር ይልቅ እንደሚወዱ መፈተኛ

- ከምድር ፍሬ ሁሉ የመጀመርያውን ( ዘጸ23፥19)፤
- ከእህል መከር የመጀመርያውን (ዘሌ 23፥10)
- ከእንስሳትከተወለዱትየመጀመርያውን (ዘኍ 8፣ 18)
- ከእስራኤልም ልጆች ሁሉ መጀመርያ የሚወለደው ለእርሱ የተቀደሰ ነበር (ዘኍ 8፣ 18)

## 2. አሥራት፡-

➢ በእርሻቸው በየአመቱ የሚያገኙትን የዘር ፍሬ፤ የወይን ጠጅና፤ዘይት 1/10 ኛውን በእግዚአብሔር ፊት( መገናኛው ድንኳን ፊት መብላት፣(ዘዳ14፥22)

➢ ይበሉ ዘንድ ይጠግቡም ዘንድ ለሌዋዊው፣ ለመጻተኛውም፣ ለድሀ

አደጉም፣ ለመበለቲቱም መስጠት (ዘዳ 26፡ 12)

ዓላማው፡-

- ✓ እግዚአብሔርን መፍራት ይማሩ ዘንድ( ዘዳ14፡23, 8:17)

- ✓ የእጃቸውን ሥራ ሁሉ ይባርክላቸው ዘንድ (ቁ.29)

## 3. ቸርነት/ምጽዋት

ዓላማው፧-

- ✓ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገውን ርህራሄ ለማስታወስ (ዘሌ19÷10 ፣ 23÷22)

- ✓ በእግዚአብሔር ዘንድ ለማከማቸት እና ብድራትን ለመቀበል (ምሳ 19፧17፣ ሉቃ14:13)፣

**መመርያ** (ማቴ 6፤3-4)

**በብሉይ ዘመንም በፍቃደኝነት መስጠት ይበረታታ ነበር፡ (ዘጸ25፡2፣ 35፤21)**

## መስጠት በአዲስ ኪዳን

1. **ጌታኢየሱስ እንድንሰጥ ይፈልጋል፣ ይጠብቅብናልም** (ማቴ 6፡2)፡፡
   **“ምጽዋት ስታደርግ” አለ እንጂ “ማድረግ ከፈለግህ” አላለም**

2. **የምንሰጥበት ምክንያት ጤናማ እንዲሆን ይፈልጋል** (6፡1)

3. የሰማዩ አባታችን በስውር እንደሚያየን እና እንደሚከፍለን ነግሮናል (ቁ.3-4)

4. ሐዋርያዊ ድንጋጌ ነው

(1ቆሮ 16፡1)

5. እግዚአብሔርን ማምለክ ነው

(2ሳሙ 24፡24)

- ❖ በሳምንቱ በፊተኛው ቀን

  (1ቆሮ 16፤2፣ ሐዋ20፡7)

- ❖ የተወደደ የመአዛ ሽታ ያለው የአምልኮ፣መስዋዕት፤

- ❖ ለእግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘው ስጦታ ነው፡፡

  (ፊል 4፡18፣ ዕብ 13፡16)

6. ሕጻናትና መበለቶችን መርዳት እውነተኛ አምልኮ ነው፡፡( ያዕ1፤27)

# ማነው መስጠት ያለበት ?

- ✓ ሁሉም አማኞች መስጠት ይገባቸዋል
- ✓ ለአማኞች ብቻ የተሰጠ እድል ነው
- ✓ በአማኞች ላይ ብቻ የተጣለ ኃላፊነት ነው መስጠት ማመስገን ነውና
- ✓ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለሰጠን እሱን ማስደሰት( ማመስገን) ይገባል

- ○ከማያምኑ ሰዎች ግን ስጦታን መቀበል ተገቢ አይደለም

# የተሳሳተ የመስጠት ዝንባሌ

- ግብዝነትና ኩራት ማቴ 6፡1-4

- የጥፋተኝነት ስሜት፡- ብዙ ሀብት ስላለኝ ካልሰጠሁ ሀብቴ ላይ ወይም እኔ ላይ አንዳች ችግር ይፈጠራል ብሎ ማሰብ

- ስግብግብነት ፡- ኑሮዬ ይበቃኛል ሳይል መስጠትን ሁል ጊዜ ለትርፍ ብቻ በማሰብ መስጠት ፤( ሁልጊዜ ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ መጠቀም ሉቃ 6፡38)

- በግፊት፤ በተጽእኖ መስጠት (2ቆሮ 9፡7)

➢ **በመታለል መስጠት**

መታለል= ስግብግብነት + ግፊት

➢ **ሥልጣን ኃይል ፍለጋ**

(ሐዋ 8፡8-24፣ ያዕ 2፡1-9)

## የመስጠት ትክክለኛ ዝንባሌዎች

•

❖ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለሰጠኝ ነው የምሰጠው (ያዕ 1፡17፣ ኤፌ 1፡3፤ 1ጢሞ6፡17

❖ እርሱን ደስ ለማሰኘት፤ለጸጋው ምላሽ መስጠት ነው

❖ ለእግዚአብሔር ምስጋና ክብር ማምጫ ነው (2ቆሮ 9፡13)

- ልቤ ከእግዚአብሔር ጋር በትክክል መሂዱን ምመረምርበት ነው፡፡ (ማቴ 6፡2)

- አምላክ በሕይወቴ ላይ የበላይ ገዥ መሆኑን ማረጋግጥበት ነው፡፡ (ማቴ 6፡24)

- እግዚአብሔር በሕይወቴ፤ በኑሮዬ ላይ ሲገለጥ ሲሠራ ለማየት ነው (2ቆሮ9፡10)

- በሰማይ መዝገብ ለማከማቸት ነው (ማቴ 6፡4.19-20፣ 1ጢሞ 6፡19)

- በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ለመለማመድ (2ቆሮ9፡8-11)

- ለእግዚአብሔር ፍቅርን ለመግለጥ (1ዮሐ3፡17፣ ያዕ2፡15-17)

- አስቀድሞ ራስን ለጌታና ለአገልግሎቱ በመስጠት

- ያለምንም ሐዘን

- በደስታ

- ያለምንም ግዴታ

- በልብ እንዳሰቡ መጠን

በብዛት የሚሰጥ በብዛት ያጭዳል
በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ያጭዳል